በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No 7/ኀ1/2/9
ቀን
Date 23/11/2011

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>መመሪያ መላክን ይመለከታል</u>

ከሐምሌ 2008 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለውን የገቢ ግብር አዋጅ በተሟላ የሕግ ማዕቀፍ ተፈፃሚ ለማድረግ በአዋጁ ለገንዘብ ሚኒስቴር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በመ/ቤታችን እንዲወጡ ከሚጠበቁ 11(አስራ አንድ) መመሪያዎች መካከል ከዚህ በፊት ከላክንላችሁ 7 (ሰባት) መመሪያዎች በተጨማሪ የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣውን መመሪያ ቁጥር 8/2011 ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን ስለሆነ ከነሐሴ 1 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ መመሪያው በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

Letter B/GT

ስልክ
Tel 251-11-155 24 00,22 66 98
251-11-155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ
P.O.Box 1905,1037
እባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ
Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia

# የገንዘብ ሚኒስቴር

## የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2011

ገንዘብ ሚኒስቴር

2011 ዓ.ም

## የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2011

1. <u>አውጪ ባለሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስቴር በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/ 2008 አንቀጽ 99(2) እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 56(1) በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

2. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ 'የካፒታል ሃብቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 8/2011' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. <u>ትርጓሜ</u>

በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር በገቢ ግብር አዋጁ እና በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም፡-

1. “ግብር የሚከፈልበትን ሃብት በማስተላለፍ የተገኘ ጥቅም” ማለት ሀብትን በማስተላለፍ የተገኘው የገንዘብ መጠን ሃብቱ እስከተላለፈበት ጊዜ ድረስ ከወጣበት ወጪ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን ሲሆን፣ መብትን ወይም ምርጫን በማስተላለፍ የሚገኝን ጥቅም ይጨምራል፡፡

2. “ምድብ “ሀ” ግብር የሚከፈልበት ሀብት” ማለት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 59(7)(ለ) እና አንቀጽ 2(13) መሰረት የማይንቀሳቀስ ሀብት ሲሆን በማዕድን ወይም በነዳጅ ሀብት ላይ ያለን መብት ወይም የማዕድን ወይም የነዳጅ መረጃዎችን ይጨምራል፡፡

3. "ምድብ "ለ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት" ማለት በፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 59(7)(ሐ) ላይ በተገለጸው መሰረት አክስዮኖችና ቦንዶች ናቸው፡፡

4. "ለሀብት የሚደረግ ወጪ" የሚለው ሀረግ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 68 ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

5. "ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ" የሚለው ሀረግ በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 70 ላይ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡

6. "አክሲዮን ማስተላለፍ" ማለት በአክሲዮን ማህበር፣ ኃላፊነቱ በተወሰነ የግል ማህበር ወይም በሽርክና ማህበር ውስጥ ባለ አክሲዮን የነበረ ሰው አክስዮኑን በሽያጭ ወይም በስጦታ ማስተላለፍ ነው፡፡

7. "ባለስልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር ወይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ወይም የድሬዳዋ አስተዳደር የገቢዎች ባለስልጣን ነው፡፡

8. "አዋጅ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ነው፡፡

9. "ደንብ" ማለት የፌደራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ነው፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ የምድብ 'ሀ' እና የምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ ጥቅም በሚያገኙ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## <u>የካፒታል ሀብቶች በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ግብር ስለመክፈል</u>

5. <u>የግብር መጣኔ</u>

በአዋጁ አንቀጽ 59 በተደነገገው መሰረት አንድ ሰው በምድብ 'ሀ' ወይም በምድብ 'ለ' የተጠቀሱ ሀብቶችን በማስተላለፍ ጥቅም ያገኘ እንደሆነ በተገኘው ጥቅም ላይ እንደቅደም ተከተላቸው 15 በመቶ ወይም 30 በመቶ ግብር ይከፍላል፡፡

6. <u>የግብር ስሌት</u>

1. በአዋጁ አንቀጽ 21(4) በተደነገገው መሠረት አንድ የንግድ ስራ ሀብት በአዋጁ አንቀጽ 59 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ከሆነ የንግድ ስራ ሀብቱን በማስተላለፍ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ከንግድ ስራው ሀብት የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው ለንግድ ስራው ሀብት የተደረገው ወጪ በንግድ ስራው ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ ለንግድ ስራ ሀብቱ ከተደረገው ወጪ በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 59 እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግብር የሚከፈልበት ይሆናል፡፡

2. በአዋጁ አንቀጽ 59 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሙሉ ለሙሉ ለቤት ኪራይ አገልግሎት ውሎ የነበረ እንደሆነ ሀብቱን በማስተላለፍ ከሚገኘው ገቢ ውስጥ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው ለሀብቱ የተደረገው ወጪ በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ ለሀብቱ ከተደረገው ወጪ በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 59 እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

3. የካፒታል ሀብትን በማስተላለፍ ከተገኘው ጠቅላላ ጥቅም ውስጥ በንግድ ስራ ገቢ ወይም/እና በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተተው እና በአዋጁ አንቀጽ 59 መሰረት ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን ቀጥሎ በተመለከተው ቀመር የሚሰላ ይሆናል፡፡

   ረ= ሀ-(ለ+መ)
   ሠ= ለ - ሐ

   ለዚህ ቀመር አፈጻጸም፡-

   ሀ) ሀብቱ የተሸጠበት ዋጋ
   ለ) ሀብቱ የተገኘበት /የተገዛበት ዋጋ (ለሀብቱ የተደረገ ወጪን ጨምሮ)
   ሐ) የሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ
   መ) የግሽበት ማስተካከያ
   ሠ) ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ጠቅላላ ጥቅም ወይም ከደረሰ ኪሳራ ውስጥ በንግድ ስራ ገቢ ወይም/እና የቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ገቢ ወይም ተቀናሽ የሚደረግ ኪሣራ
   ረ) ከሀብቱ ሽያጭ ከተገኘ ጥቅም የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ ግብር የሚከፈልበት ገቢ

4. ግብር የሚከፈልበት ሀብት ለንግድ ስራ እና ለኪራይ አገልግሎት ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆነ ከሀብቱ የተጣራ የመዝገብ ዋጋ የሚበልጠው ለሀብቱ የተደረገው ወጪ ሀብቱ በተሸጠበት ጊዜ ለንግድ ስራ እና ለኪራይ አገልግሎት በዋለው መጠን ልክ ተከፋፍሎ በንግድ ስራ ገቢ እና በቤት ኪራይ ገቢ ውስጥ የሚካተት ሲሆን፣ ለሀብቱ ከተደረገው ወጪ በላይ በሚገኘው ጥቅም ላይ በአዋጁ አንቀጽ 59 እና በዚህ መመሪያ መሰረት ግብር ይከፈልበታል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም በደንቡ አንቀጽ 56(1) መሰረት የሚተላለፈው የምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲሆን ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረጋል፡፡ ሆኖም የምድብ 'ለ'ግብር የሚከፈልበት ገቢን ለማስላት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የሚደረገው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያሰራጨውን አመታዊ አማካይ የዋጋ ግሽበት መጣኔ መረጃ መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡

7. የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የሚቀነሰው በሠንጠረዥ 'ሐ' ወይም/ እና 'ለ' ውስጥ የሚካተት ገቢ ከተለየ በኋላ ነው፡፡

8. ለካፒታል ሀብት የተደረገ ወጪ ከንብረቱ ዋጋ 20% ያነሰ በመሆኑ ምክንያት በወጪነት የተያዘ ከሆነ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም በሚሰላበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ከግምት ውስጥ አይገባም፡፡

7. <u>የንግድ ድርጅት ሲተላለፍ ሊቀርብ ስለሚገባ ሰነድ</u>

1. የንግድ ድርጅት በሚተላለፍበት ጊዜ ከድርጅቱ ጋር አብረው የሚተላለፉ ንብረቶችን የመዝገብ ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ መቅረብ አለበት፡፡

2.. ግብር ከፋዩ የሚተላለፉትን ንብረቶች ዋጋ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻለ አግባብነት ያለው ፈቃድ በተሰጠው ንብረት ገማች የተገመተውን ንብረቱ የተገዛበትን ዋጋ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

8. <u>ሀብትን በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢን ለማስላት መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች</u>

1. የሂሳብ መዝገብ የሚይዝ ግብር ከፋይ ለካፒታል ሀብቱ የተደረገውን ወጪ የሚከተሉትን ማስረጃዎች በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት፡፡

   ሀ) ለሀብቱ የተደረገውን ወጪ እና ሀብቱ የተገኘበትን ጊዜ የሚያሳይ ሰነድ፣

   ለ) ሀብቱ ከተገኘበት ጊዜ ጀምሮ ስለእርጅና በጠቅላላው ተቀናሽ የተደረገውን ገንዘብ የሚያስረዳ ሰነድ

2. ግብር ከፋዩ ሀብትን በማስተላለፍ ያገኘውን ገቢ አግባብነት ባለው ማስረጃ ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን፣ በቀረበው ማስረጃ መሰረት ግብሩ የሚከፈለው ማስረጃው በባለስልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

3. ለካፒታል ሀብቱ ስለተደረገው ወጪ እና የካፒታል ሃብቱን በማስተላለፍ ስለተገኘው ገቢ በግብር ከፋዩ የቀረበው ማስረጃ በባለስልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 3 መሰረት የካፒታል ሀብትን በማስተላላፍ የተገኘው ጥቅም ይሰላል፡፡

4. የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም እንዲይዝ ግዴታ የሌለበት ግብር ከፋይ ሀብቱ የተገኘበትን ዋጋ በሚመለከተው አካል አስገምቶ እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ ይህን አስገምቶ ካላቀረበ ግብር ከፋዩ ወጪ እንደሌለው ይቆጠራል፡፡

5. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 አፈጻጸም 'አግባብነት ያለው ማስረጃ' ማለት ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የሚቀርብ ውል ሲሆን በውሉ ላይ የተጠቀሰው የመሸጫ ዋጋ ተቀባይነት የሚያገኘው ከወቅቱ የገበያ ዋጋ ጋር ተመጣጣኝ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡

## 9. <u>በቤት አልሚዎች የሚተላለፍ ቤት</u>

ቤት ገንብተው በሚሸጡ የቤት አልሚዎች ላይ መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆነው የተላለፈው ቤት ባለቤትነት አስቀድሞ በቤት አልሚው ስም የተመዘገበ  እንደሆነ ብቻ ነው፡፡

## 10. <u>የማይንቀሳቀስ ሀብት ስለማስተላለፍ</u>

1. ግንባታው ያልተጠናቀቀ ወይም ሁለት አመት በመኖሪያነት ያላገለገለ የማይንቀሳቀስ ሀብት የተላለፈ እንደሆነ በማስተላለፍ ከሚገኝ ጥቅም ላይ በአዋጁ መሰረት 15 በመቶ ግብር ይከፈልበታል፡፡

2. ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አፈጻጸም የማይንቀሳቀሰው ሃብት ፕላን የመኖሪያ ቤት የሚል ቢሆንም በቤት ቁጥሩ ንግድ ፈቃድ የወጣበትና ለንግድ አገልግሎት ሲውል የነበረ ከሆነ በአዋጁ መሰረት 15 በመቶ ግብር ይከፈልበታል፡፡

## 11. <u>የኩባንያዎች የአክስዮን ሽያጭ ገቢ</u>

ኩባንያዎች ያወጡትን አክስዮን ከዋጋው በላይ በመሸጥ የሚያገኙት ገቢ በሰንጠረዥ "ሐ" መሰረት ግብር የሚከፈልበት  ሲሆን፣ በአዋጁ አንቀጽ 64(1)ሀ መሰረት ይህ ጥቅም የካፒታል ሀብቶችን በማስተላላፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚጣለው ግብር ተፈጻሚ አይደረግበትም፡፡

## 12. ለባንክ ዕዳ መክፈያ ስለተያዘ የማይንቀሳቀስ ሃብት

ባንኮች በዋስትና የያዙትን የማይንቀሳቀስ ሃብት ለብድር ዕዳ ማስመለሻ በሚያውሉበት ወቅት ንብረቱ ሲሸጥ ሊከፈል የሚገባው የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ተፈጻሚ የሚሆነው ከንብረቱ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ባንኮች የሰጡትን የብድር ገንዘብ ከሸፈነ በኃላ ቀሪ ገንዘብ ካለ ብቻ ነው፡፡

## 13. ሀብትን በስጦታ ስለማስተላለፍ

"ምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም "ምድብ "ለ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት በስጦታ ሲተላለፍ ስጦታ ተቀባዩ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ግብር ይከፍላል፡፡ ግብሩ የሚሰላው በደንቡ አንቀጽ 53 መሠረት በስጦታ ከተላለፈው ሀብት የገበያ ዋጋ ላይ ለሀብቱ የተደረገው ወጪ ከተቀነሰ በኂላ በሚቀረው የገቢ መጠን ላይ ነው፡፡

## 14. ሀብትን በውርስ ስለማስተላለፍ

"ምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት በውርስ ሲተላለፍ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ገቢ ግብር አይከፈልበትም፡፡

## 15. ሀብትን በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የግብር አከፋፈል ሁኔታ

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 44 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ 'ምድብ 'ሀ' ግብር የሚከፈልበት ሀብትወይም 'ምድብ 'ለ' ግብር የሚከፈልበት ሀብት ሲተላለፍ ግብር ከፋዩ ሊከፈል የሚገባውን ግብር በቀጥታ ለባለስልጣኑ ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## 16. ዕጣን ወይም ድርሻን ስለማስተላለፍ

በሕብረት ስራ ማህበር ውስጥ በባለቤትነት የተያዘ ዕጣ ወይም ድርሻ በሚተላለፍበት ጊዜ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ በሚገኝ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 17. የሽያጭ/የስጦታ/የልውውጥ ውል መፍረስ

"ምድብ "ሀ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት ወይም 'ምድብ "ለ" ግብር የሚከፈልበት ሀብትን ለመሸጥ/በስጦታ ለመስጠት/ለመለዋወጥ የተደረገው ውል ሲፈርስ የካፒታል ሃብት በማስተላለፍ ከሚገኝ ገቢ ላይ የተከፈለው ግብር ተመላሽ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግብር ከፋዩ የከፈለው ግብር ተመላሽ እንዲደረግለት ለታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄ ማቅረብ የሚችለው ግብሩ ከተከፈለ በኂላ ባለው የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩልዩ ድንጋጌዎች

18. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ስለትክክለኛ የዕቃ ወይም የአገልግሎት የገበያ ዋጋ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 3 በተደነገገው መሠረት የአሠራር ሥርዓት እስከሚዘረጋ ድረስ ባለስልጣኑ ሲጠቀምበት የነበረው አሰራር ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

19. የተሻረ መመሪያ

በገቢዎች ሚኒስቴር ሰኔ 11/1995 በቁጥር 01/አ21/1/2 የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ በሚገኝ ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር አፈጻጸም የወጣው መመሪያ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

20. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከ ነሐሴ 1 ቀን 2011 ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ _______ ቀን 2011 ዓ.ም.

አህመድ ሺዴ
የገንዘብ ሚኒስትር